የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፭
አዲስ አበባ ህዳር ፳፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No.5
ADDIS ABABA, 1st December 2017

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፪/፪ሺ፲
በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በመደበኛ የባቡር ኔትወርክ ዝርጋታ፣ አሰራር እና አስተዳደር ዙሪያ የተደረገዉን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ……………………………………………ገፅ ፱ሺ፱፻፷

CONTENT

PROCLAMATION NO.1052/2017
Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Sudan for the Development, Operation and Management of Standard Gauge Railway Network Ratification Proclamation ……………….page 9960

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፪/፪ሺ፲

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል መደበኛ የባቡር ኔትወርክ ዝርጋታ፣ አሰራር እና አስተዳደር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በመደበኛ የባቡር ኔትወርክ ዝርጋታ፣ አሰራር እና አስተዳደር ስምምነት በካርቱም ህዳር ፳፭ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህን ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሰት አንቀጽ ፶፭ /፩/ እና /፲፪/ መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION No.1052/2017

## A PROCLAMATION TO RATIFY AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF SUDAN FOR THE DEVELOPMENT, OPERATION, AND MANAGEMENT OF STANDARD GAUGE RAILWAY NETWORK

**WHEREAS,** the Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Sudan for the Development, Operation and Management of Standard Gauge Railway Network has been signed on December 4 , 2013 in Khartoum;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the Agreement at its session held on of 2nd November day of 2017;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ “በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በመደበኛ የባቡር ኔትወርክ ዝርጋታ፣ አሰራር እና አስተዳደር ዙሪያ የተደረገዉን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፶፪/፪ሺ፲” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ህዳር ፳፭ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም በመደበኛ የባቡር ኔትወርክ ዝርጋታ፣ አሰራር እና አስተዳደር ዙሪያ የተደረገዉ ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>አስፈጻሚ አካላት</u>**

ይህን ስምምነት እንዲያስፈጽም የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትራንስፖርት ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር ፳፪ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the “Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Sudan for the Development, Operation and Management of Standard Gauge Railway Network Ratification Proclamation No1052/2017’’.

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Sudan for the Development, Operation and Management of Standard Gauge Railway Network, signed on December 4, 2013 is hereby ratified.

**3. <u>Implementing Organs</u>**

The Ministry of Transport of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby empowered to implement the Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force up on publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 1st day of December 2017.**

**MULATU TESHOME (DR.)**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**